አማርኛ أمهرية

# 3 የተዉሒድ ክፍሎች

ለእርሱ ለሌላ ለማንም የማይገቡ በጌትነቱ፣ በአምላክነቱና  በስሞቹና ባህርያቱ አሏህን (عزوجل) መነጠል

በ3 ይከፈላል

## ተዉሒዱ አር-ሩቡቢያ (አሏህን በጌትነቱ መነጠል)

እሱም አሏህን (عزوجل) በተግባራቶቹ ወይም እርሱ ባስገኛቸዉ ነገራቶች፣ በበላይነቱና በማስተናበሩ መነጠል ነዉ.

## ተዉሒዱ አል-ኡሉሒያ (አሏህን በአምልኮቱ መነጠል

እሱ አሏህን (عزوجل) በአምልኮ ወይም አምልኳዊ ድርጊቶች መነጠል ነዉ.

## ተዉሒዱ አል-አስማኢ ወስ-ሲፋት (አሏህን በስሞቹና ባህሪያቱ መነጠል)

አሏህ (عزوجل) በኪታቡ ወይም በመልክተኛዉ እንደበት ራሱን በሰየመዉና በገለፀዉ እርሱን መነጠል ነዉ። ይህም እርሱን ለራሱ ያፀደቀዉን በማፅደቅ እና ከርሱ በጠረዉ ደግሞ በማጥራት ያለማንሻፈፍ፣ ያላማራቆት፣ እንዴትነትን ያለማድረግና ያለማመሳሰል ነዉ የሚሆነዉ።

# ሶስቱ የዲናችን እርከኖች

## አል እስላሙ

አሏህ ለርሱ ብቻ በመገዛት እጅ እግርን መስጠት፣ ለትዕዛዛቱ መጎተትና ከጣዖት አምልኮትና ባለቤቶቿ መፅዳት ነዉ

የእስልምና መሰረቶች 5

1- ሁለተ ሸሃዳ
2- ሶላትን ማቆም
3- ዘካን መስጠት
4- ረመዷንን መፆም
5- ለቻለ ሰዉ ሀጅን ማድረግ

## አል-ኢማን

በምላስ የሚባል፣ በልብ የሚቋጠርና በአካላት የሚሰራ ሆኖ፣ ይጨምራል ይቀንሳልም

የኢማን ምሰሶዎች (መሰረቶች) 6

1- በአሏህ ማመን
2- በመላኢኮቹ ማመን
3- በመፅሃፍቶቹ ማመን
4- በመልዕክተኞቹ ማመን
5- በመጨረሻይቱ ቀን ማመን
6- በቀደር፣ ጥሩም ይሁን መጥፎዉ ማመን

## አል እህሳን

አሏህን እንደሚታያዉ ሆነህ ማምለክ ነዉ፣ አንተ ባታየዉም እርሱ ያየሃልና

አንድ መሰረት፣ ሁለት ደረጃዎች አሉት

1- ኢባደቱ አል-ሙሻሀደ :- አሏህን እንደሚታየዉ ሆነ ማምለክ

2- ኢባደቱ አል-ሙራቀበ:- አንተ ባታየዉ እርሱ ያየሃል

# 4 የተከለከሉ ነገሪቶች ክፍሎች

## ትናንሽ ወንጀሎች

ከትላልቅ ወንጀሎች ዉጭ የሆኑ ናቸዉ። ትልቅ ወንጀሎች ንስሀ በመግባት (ተዉባ በማድረግ/ ይማራሉ፣ ትናንሾቹ ግን ተጠራቅመዉ ትልቅ ይሆናሉ። ነብዩ ﷺ "ትናንሽ ወንጀሎችን ተጠንቀቋት፣ ሰሪዉ ግለሰብ ላይ ይጠረቃቀማሉ፣ እስኪያጠፉት ድረስ" አሉ።

## ትላልቅ ወንጀሎች

ያረሱ የሆነ ቅጣት የተደነገገለት ነዉ። ድግምት፣ ወላጆችን አለማክበር፣ ወለድ መብላት፣ ዝሙት፣ ግብረ ሰዶማዊነት፣ ዉሸት፣ አስካሪ መጠጥ፣ ሌብነት፣ ሀሜት፣ አሏህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለፍትህ መግደል ወዘተ ናቸዉ።

## ትንሹ ሽርክ

ከእስልምና አያስወጣም፣ ግን ከትላልቅ ወንጀሎች ትልቁ ነዉ። አሏህ ካለ እና አንተም ካልክ ማለትን ይመስል፣ ከአሏህ ዉጭ ባለን መማል፣ ይሉንታና፣ በገድ ማመን፣ ህርዝን ማንጠልጠል ወዘተ ከመጥፎ ነገር ወይም ከቡዳ ይከላከላሉ ብሎ ማድረግ ናቸዉ።

## ትልቁ ሽርክ

ከእስልምና ያወጣል። ስምትም ምህረት አይጠየቅለትም። ልክ አሏህን እንደሚጣራ ሁሉ ብጤን አድርጎለት መጣራት፣ ወይም መፍራት ወይም መከጀል ወይም ለአሏህ ብቻ መሆን ያለበት አይነት ዉዴታን መዉደድ፣ አልያም ደግሞ ከኢባዳዎች አይነት የሆነን አሳልፎ መስጠት